# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ገቢዎች ቢሮ

## የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር አገቢ 12/2011

መስከረም 2011ዓ.ም

ባህር ዳር

የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዲወሰን በህግ የተደነገገ በመሆኑ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፍልበትን አሠራር በመመሪያ መወሰን በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ የገቢ ግብር አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 162/2010 አንቀጽ 66 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የንግድ ሥራ** ከተቋረጠ **በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 12/2011**"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1) **"የንግድ ሥራ ማቋረጥ"** ማለት በታክስ ከፋይነት ተመዝግቦ የንግድ ሥራ ሲሠራ የነበረና የንግድ ሥራውን ማቆሙን በጽሁፍ ለገቢዎች ቢሮ በማስታወቅ ከታክስ ከፋይነት የተሰረዘ ሰው ነው፡፡
2) **" ገቢዎች ቢሮ "** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ማለት ሲሆን በየደረጃው እርከን የሚገኙ የገቢ ተቋማትንም ይጨምራል፡፡፤
3) **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ነው፡፡
4) **"ደንብ" ማለት** የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 162/2010 ነው፡፡
5) በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ባገኘ ታክስ ከፋይ ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

4. **የንግድሥራ ከተቋረጠ በኋላ ስለሚገኝ ገቢ**

ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ሊያገኝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራውን ካቋረጠ በኋላ የካፒታል እቃዎችን ጨምሮ በእጁ የሚገኙትን ያልተሸጡ እቃዎች በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ፣
2) በንግድ እንቅስቃሴ ወቅት ሊሰበሰብ የማይችል ገቢ ነው ተብሎ የተሰረዘ ገቢ የንግድ ሥራው ከተቋረጠ በኋላ ሲሰበሰብ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ገቢዎች ቢሮ